# መ ዘ ክ ር ፤

ሰዎች ፡ በተፈጥሮ ፡ እኩል ፡ የመሆናቸውን ፡ ያህል ፡ ለምድራቱም ፡ ሀብት ፡ የተቀራረበ ፡ ድርሻ ፡ እንዲኖራቸው ፡ በማሰብ ፤ የምጣኔ ፡ ሀብት፡ ፍትሕ ፡ (ECONOMIC JUSTICE) ይደረግላቸው ፡ በማለት ፡ በየሀገሩ ፡ የጮሁ ፡ ሰብአውያን ፡ ሁሉ ፡ የአቤቱታቸው ፡ ውጤት ፡ እንደምኞታቸው ፡ ያልተሳካ ፡ በመሆኑ ፡ ሁልጊዜ ፡ ያዝናሉ። ይህ ፡ ጩኸት ፡ ለጠቅላላው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ዘር ፡ሙሉ ፡ ደኅንነት ፡ ሲባል ፡ በዓለም ፡ አቀፍ ፡ ደረጃ፡ የሚደረግ ፡ የድሆች ፡ እሪታ ፡ ነው ። በቀረው ፡ ዓለም ፡ እንደሆነው ፡ ሁሉ ፡ በሀገራችንም ፡ ይህ ፡ አቤቱታ ፡ አስፈላጊውን ፡ መልስ ፡ ለማግኘት ፡ ባለመቻሉ ፡ ለብዙ ፡ ችግረኞች ፡ሕይወት ፡ መጥፋት፡ ምክንያት ፡ ሆኗል ። ይህችም ፡ ግጥም ፡ የዚሁ ፡ ዓለም ፡ አቀፋዊ ፡ አቤቱታ ፡ ተልእኮ ፡ ተካፋይ ፡ በመሆኗ ፡ መዘክርነቷ ፡ ለነዚሁ ፡ በችግር ፡ ምክንያት ፡ ላለቁት ፡ ሙታንና ፡ ለሚያልቁትም ፡ ግማሽ ፡ ሕያዋን ፡ ነው ።



# እ ል ፌ ት ፤

የግጥሞቼን ፡ ደራሲነት ፡ አይንፈገኝ ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሺ ፡ ቅጂዎችን ፡ ካሳተምሁ ፡ በኋላ ፡ ማንኛውም ፡ ሰብአዊ ፡ ፍጡር ፡ ቢሆን ፡ እንደፈለገው ፡ ቢያደርጋቸው ፡ አለመቃወሜንና ፡ በዚሁም ፡ ውሳኔዬ ፡ መሠረት ፡ አሳልፌ ፡ መስጠቴን ፡ አረጋግጣለሁ ።



Abebe Kirub

# በረከት መርገም ፡

ዝንተ ፡ ዓለም ፡ ሲገዝፍ ፤ ከኢ.ምንት ፡ ኑባሬ፤ ምንት
ነት፡ ተገኝቶ ፡ ሕይወት ፡ ሲውተረተር ፡
ያኔ፡በፍጥረት ፡ ቀን፡ የሀላዌ ፡ አልፋ ፤ ሀልው ፡ ሲቆረቆር፡
ከፍጥረት ፡ አንደኛው - ያ ፡ ትልቁ ፡ ፍጡር -
ሰው ፡ እየተባለ ፡ ባለም ፡ ውስጥ ፡ እንዲኖር ፡
በሕይወት ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፡ ስሙ ፡ ቀልሞ ፡ ነበር ።
እንዳፈጣጠሩ ፡ እንደአመጣጡ ፡ እንደተሰጥዎው ፡
ተመዛኝ ፡ ከሆነ ፡
በሥነ ፡ ፍጥረት ፡ ውስጥ ፡ ማነው ፡ ከቶ ፡ እንደሰው ፡
የተሽሞነሞነ ፡
ወገኛ ፡ ተብሎ ፤ ከኀሊና ፡ ጋራ ፤ ተሞሽሮ ፡ ሊኖር ፥
በክብር ፡ የሰፈነ ፡ በግብር ፡ የገነነ ።
ግና ፡ ምን ፡ ይሆናል )
የሆነውን ፡ ትቶ ፡ ላለመሆን ፡ ሲሻ ፡ አጉል ፡ ሲቀናጣ ፡
ሌላ ፡ ሆኖ ፡ ቀርቷል ።

የሱነቱን ፡ ትቶ ፤ ምንነቱን ፡ ንቆ ፡ ሌላ ፡ በመሆኑ ፤
ልረግመው ፡ ተነሣሁ፡ የኔው፡ ስለሆነ፤ ያንደኛው፡ ፊት ፡ጎኑ፡
ከምንጅላት ፡ ሐረግ ፡ ቅርንጫፉን ፡ ይዞ ፤ ሲሳሳብ ፡ ወገኑ ፤
ተጽፎ ፡ እንዳለው ፡ በመጣፉ ፡ ባልቴት ፤ «ከወፍራም ፡
ማይ ፡ ይልቅ ፡ የደም ፡ ነው ፡ ሚዛኑ» ።

ስለዚህ ፡ ልጀምር ፤ የርግማኔን ፡ ሀሁ ፤ የመርገሚን ፡አሊፍ ፤
ምናልባት ፡ ቢያበርደው ፤ የንዴቱን ፡ እሳት ፤
ተዳፍኖ ፡ ያለውን ፤ ከልቤ ፡ ስር ፡ ደጃፍ ።

ምናልባት ፡ ከናንተ ፡ ፍላጻው ፡ ጨራርፎት ፤ ቢኖር ፡
ቅር ፡ የሚሰኝ ፤
በሱነቱ ፡ ግምት ፤ በተዛባ ፡ መንፈስ ፤ መሰሉን ፡ መርገሚ ፤
ኃጥእ ፡ ነው ፡ ቢያሰኘኝ ፡
ራሴው ፡ በራሴ ፡ የኔው ፡ ገሃነም ፡ ነኝ ።

ሆኖም፤ ምሥጢሩ ፡ ባይገባም ፤ ላያሌ፡ ዘመናት ፤ በአ
ንክሮ ፡ ምጥቀት ፤ ስናየው ፡ የኖርነው፤
ሲነድ፡ ሲቃጠል ፤ የማይሞቅ፡ እሳት ፡ ነው ።
ርግጥ፡ ነው፡ ክቡራን፡እውነት፡ ነው፡ ክቡራት፡ እኔ ፡
በበኩሌ ፤ አልወድም ፡ ነበረ ፤ ሰውን ፡ ያህል ፍጡር ፡
ዳዊትና ፡ ዳርዊን ፡ ያፀደቁለትን ፡ ያንን ፡ ትልቁን ፡ ትል ፡
መወረፍ ፡ መጣቆስ ፤

አሁን፡ግን፡ ሳልፈልግ፡የትዝብቱ፡ግፊት፤እየጎነተለ፤ኮር
ኩሮ፡አስነሣኝ ፡ያላግባብ ፡ አላውሶ፡ ምላሴን፡ ሊያስለቅስ።
ከምን ፡ ላይ ፡ ልጀምር ፤ ከየትስ ፡ ልነሣ ፡
በየግንባሩ ፡ ላይ ፤ ለጥፎ ፡ ለማኖር ፡ የትዝብት ፡ ወቀሳ ።

አዎን ፡ የተዛባን ፡ መንፈስ ፡ ያኀበጠን ፡ ኑሮ ፡ የገለማን
ሕይወት ፤ ምክንያቱ ፡ ሆነው ፡ ካስገኙ ፡ በዓለም ፤
ተራው ፡ ምን ፡ አረገ ፤ ሊቆቹን ፡ ነው ፡ መርገም ።



እንግዲህ ፡ ጆሮ ፡ ሆይ ፤ ለበረከት ፡ ያህል ፤ መርገሜን ፡
ስጀምር ፤
በሊቃውንቱ ፡ ነው ፤ በነዚያ ፡ ሀካዮች ፤ ተፈጥሮን ፡ አጣ
መው ፡ ባደረጉት ፡ ገባር ፡
እንግዲህ ፡ ልጀምር ፤ በነሱው ፡ ላንገራግር ።

በዓየር ፡ ዕርዳታ፤ጥረህ፡ተጣጥረህ፤ታግለህ፡ያገኘኸው፡
አሠሡን ፡ ገሠሡን ፤ ልቅምቃሚ ፡ ወሬ ፤ እንቶ ፡ ፈንቶ ፡
ተረብ ፤ ከሥፍራ ፡ ወደ ፡ ሥፍራ ፤ ለማዛመት ፡ ለሰው ፤
ምኞትና ፡ ተስፋን ፤ ድለላን ፡ ፍራቻን ፡ ለመስበክ ፡ለመላው
ሬዲዮ ፡ ስትፈጥር ፤ ለውሸት ፡ ማወጃ ፤ እንዲሆን ፡ አስ
በህ ፤ ከሆነ ፡ የሠራኸው ፡
የዋሁ ፡ ማርኮኒ ፤ ነፍስህን ፡ አይማረው ።

በኔነት ፡ አንቀልባ ፤ ታዝለው ፡ ለሚኖሩ ፤ ላርበ ፡ ሰፌ
ዎቹ ፤ ለመሐል ፡ ሰፋሪ ፡ ለሀብታሞች ፡ ብቻ ፡ ለማበር
ከት ፡ ጥቅም ፤
በየመንገዱ ፡ ላይ ፡ ደሀን ፡ እየገጩ፤ ሕይወትን፡ ለማውደም፤
የባይተዋርን ፡ ነፍስ ፡ ያላግባብ ፡ አጥፍቶ ፡ አስፋልት ፡
ለማጨማለቅ ፡ እንደኔ ፡ ባለው ፡ ደም ፤

ደግሞም ፡ ለማጭለግያ ፡ አንዳንዷን ፡ ደማም ፤
እንዲሆን ፡ ከሆነ ፡ የተግባርህ ፡ ግቡ ፤ ለጭከና ፡ አቋም ፤
ደንቆሮው ፡ ፋራዳይ ፡ ከመኪናህ፡ ጋራ፤ ውቅያኖስ፡ሥጠም።

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እኛ ፡ እንዳየነው ፡
ሲነድ ፡ ሲቃጠል ፤ የማይሞቅ፡ እሳት ፡ ነው ።

ሥትሠሩ ፡ ከጥንቱ ፤ ያየር፡ መንኰራኵር ፤
ለመጫን ፡ ከሆነ ፡ አልባሌ ፡ ካልቸር ፤
ደግሞም ፡ ማጓጓዥ ፡ ዝባዝንኬ ፡ ነገር ፤

ምናምኑን ፡ መምጫ ፡ ከያንኪዎች ፡ ሀገር ፡ ከናጅሬ ፡ ብሔር
ሮንግ ፡ ብራዘርስ ፡ እንጦርጦስ ፡ ግቡ ፡ ካሮኖሳኑ ፡ ጋር ።

ሜሬ ፡ ለመያለት ፡ ግዳይ ፡ ለማዋሸክ ፡ ወሬ ፡ ለማ
ዛመት ፡ እንዲመች ፡ ብለህ ፡
ኮረዳን ፡ ካለሌ ፡ ደግሞም ፡ ጋለሞታን ፡ ማቃጠር ፡አስበህ ፡
ግፍን ፡ ለመማከር ፡ ጭቆናን ፡ ለማቀድ ፡ ችግርን ፡ ለማ
ወጅ ፡ በነዚህ ፡ ተመርተህ ፡
እንዲሆን ፡ ከሆነ ፡ ቴሌፎን ፡ መሥራትህ ፡
ደደቡ ፡ ግራሃም ፡ ምድረ ፡ ፋይድ ፡ ያወርድህ ።

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ስናየው ፡ የኖርነው ፡
ሲነድ ፡ ሲቃጠል ፡ የሚሖቅ፡ እሳት ፡ ነው ።

ኤሌክትሪሲቲን ፡ ለመፍጠር ፡ ስታቅድ ፤
ምግብ ፡ እንዲያበስል ፡ ብርሃንም ፡ እንዲሰጥ ፡ ሞተር ፡
ሊያንቀሳቅስ ፡ ያለውድ ፡ በግድ ፡
ከፉውም፡ ፡ እንደደግ ፡ ጨካኙም ፡ እንደቸር ፡ ባለጌው ፡
ምቀኛው ፡ ሸረኛው ፡ ቀማኛው ፡ ጨቋኙ ፡ አመፀኛው ፡
ሌላውም ፡ ሁሉ ፡ ጉድ ፡
እኩል ፡ እንዲጠቀም ፡ አስበህ ፡ እንደሆን ፡ በድካም ፡ መሥ
ራትህ ፡ ይህን ፡ የጥበብ ፡ ዓምድ ፡
ሰይጣኑ ፡ ኤዲስን፡ ባለህበት፡ ዓለም፡ ያቃጥልህ፡ ነገድጓድ።
ፍሬውን ፡ እህሉን፡ ሥጋውን ፡ ወተቱን፡ መጠጡን ፡
ቅባቱን ፤ ማቅረቢያ ፡ እንዲሆን ፡ ለናጅሬዎች ፡ ሆድ ፤
ለነዚያ ፡ ኢምንቶች ፡ በደም ፡ ለሚያመልኩ ፤ ለባለብጫ ፡
ደም ፡ ለነሆድ ፡ አምላኩ ፤ ለእንትኖች ፡ ነገድ ፡
እንዲሆን ፡ አስበህ ፡ ከሆነ ፡ የሠራኸው ፡ ባቡርና ፡ ሐዲድ፡
ጅሉ ፡ እስቲፋንስን ፡ ሲኦል ፡ የሚወርደው ፤ ጎርፉ ፡ይዞህ፡
ይውረድ ።



ከድሮ ፡ ጀምሮ ፡ ባንከሮ ፡ እንዳየነው ፡
ሲነድ ፡ ሲቃጠል ፡ የሚሖቅ፡ እሳት ፡ ነው ።
ችግርና ፡ ደዌ ፡ ከቶም፡ድንቁርና፡በምድር፡ሲፈነድቅ ፡
የሚሠራው ፡ ሞልቶ ፡ ስንቱ ፡ ተግባር ፡ ሳያልቅ ፡
የምድሩ ፡ ሳይሞላ ፡ አዳሜ ፡ ሳይረካ ፤ የጠፈሩን ፡ ማወቅ ፡
ሮኬት ፡ ሲፐትኒክ ፡ ሳታለይት ፡ ጋጋሪን ፡ እያለ ፡ በከንቱ ፡
ዝናን ፡ ለማዳነቅ ፡
ጀማሪያቸው ፡ ሆነህ ፤ ይህን ፡ በማድረግህ፡የደንቆሮቹ ፡ሊቅ፤
ጋኔሉ ፡ ጋሊሎ ፤ በሞተው ፡ ሥጋህ ፡ ላይ ፡ ይብረቅበት ፡
ሙብረቅ ።

ያታላይ ፡ የዋሾው ፡ የሌባው፡የከጂው፡የአጉራ፡ዘለሉ ፡
የኸፉው ፡ የጨቋ ፡ የቀረውም ፡ ቶሉ ፡
ጤናው ፡ ተጠብቆ ፡ ሕይወቱም ፡ እረዝሞ ፡ አልባሌ ፡
ሥራው ፡ እጅግ ፡ እንዲስፋፉ ፡
አስቦ ፡ እንደሆነ ፤ ያ ፡ ንፍጣም ፡ ሳይንቲስት ፤ ያዋቂ ፡
ከርፉፉ ፡

ኤክስሬይ ፡ የሠራው ፡ ዊልያም ፡ ወልካፉ ፡
በሕይወት ፡ እንዳለ ፡ ድምጥማጡ ፡ ይጥፋ ፡
ሞቶም ፡ እንደሆነ ፡ በርባሮስ ፡ ያውርደው ፤ ብርቱው ፡
መልአከ ፡ ሞት ፡ ነፍሱን ፡ እያዳፉ ።
ከድሮ ፡ ጀምሮ ፤ እኛ ፡ እንዳየነው ፤
ሲቃጠል ፡ የሚሖቅ ፡ ዘለዓለም ፡ እሳት ፡ ነው።
እናያ ፡ እንቶኔ ፡ በደንብ ፡ አስፋፍታችሁ ፤
ባላችሁ ፡ መሣሪያ ፤ በኃይል ፡ ተጭናችሁ ፡
ሌላኛውን ፡ ሙብት ፡ ባለመስበካችሁ ፡
በሙታን ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ ሕይወት ፡ እንዳላችሁ ፡

ቊልቢጦ ፡ ገብርኤል ፡ ዶጋመድ ፡ ያርጋችሁ ።
አሉቲ፡ዓለምን፡ለሁለት፡በማረድ፡በሐሳብ፡ከፍላችሁ ፡
ነዋሪውን ፡ ፍጡር ፡ ስታቀጣቅጡት ፡ መርዝ ፡ ነስንሳችሁ ፡
በየራሱ ፡ ባህል ፡ በግሉ ፡ አስተስተሳስብ ፡ በብሔሩ ፡
መንፈስ ፡ እንዳይኖር ፡ አርጋችሁ ፡
በዘመናት ፡ መሐል ፡ ባለም ፡ ተገኝታችሁ ፡
የዝንብ ፡ ዲሞክራሲ፡ የምሥጥ ፡ እኩልት ፡ የጅብ ፡ ብል
ጽግና፡ በሚለው ፡ ዘያችሁ ፡
የሰውን ፡ ኅሊና ፡ የአዳሜን ፡ መንፈስ ፡ በውትብትብ ፡
ጠባይ ፡ ስለበከላችሁ ፡
አዳም ፡ ወማርቆስ ፡ ከነጭፍሮቻችሁ ፡
የሚኳው ፡ ሞሐመድ ፡ ጀሐነም ፡ ያግባችሁ ።

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ስናየው ፡ የኖርነው ፡
ሲነድ ፡ ሲቃጠል ፡ የሚሥቅ ፡ እሳት ፡ ነው ።

ሊንከልን ፡ ፕሌቶ፡አሪስቶትል ፡ ጋንዲ፤የቀሩትም ፡
ሌሎች ፡ ደደቦች ፡ ሊቃውንት ፡
የጠነባ ፡ ሐሳብ ፡ መብትና ፡ ሰላም ፡ ፍርድና ፡ ነጻነት ፡
እያሉ ፡ አስተምረው ፡ ቁንጮ ፡ ቢስ ፡ ትምህርት ፡ ጭራ ፡
የለሽ ፡ እምነት ፡
በተድላ ፡ ትዝታ ፡ በሕልማዊ ፡ ሕይወት ፤ ሰውን ፡ መርዘ
ውት ፡
በረቂቅ ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡ ባሳብ ፡ በክለውት ፡
በሞት ፡ ግሎቲን ፡ ላይ ፡ ስንቱን ፡ አስቀሥፋት?
የትይ ደርሱ ፡ ይሆን ፡ የሊህ ፡ ሰዎች ፡ ነፍሳት፣
በድህና ፡ ሽንቶ ፡ ግፋቸውን ፡ አይተው፣ የሥጥሚቸው ፡
ካዘቅት ።

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እኛ ፡ እንዳየነው ፡
ሲቃጠል ፡ የሚሥቅ ፡ ዘለዓለም ፡ እሳት ፡ ነው።



ያንድን ፡ ሀገር፡ ድቀት ፡ ያልነጠረ፡ ባህል ፡ የጠነባ ፡
ልማድ ፡ የረከሠ ፡ ጠባይ ፡
ለሌላኛው ፡ ወስዶ ፡ ባግባብ ፡ እንዲሥቃይ ፡
የዋሁን ፡ ኅሊና ፡ ተቀባዩን ፡ መንፈስ ፡ ታቡላ ፡ ራዛውን ፡
ያላግባብ ፡ አማቶ ፡ አንኅል ፡ ለመበከል ፡
ከደስታ ፡ አስታከህ ፡ በፌዝና ፡ በቀልድ ፡ በቧልት ፡ በጨ
ዋታ ፡ መርዝህን ፡ ሸፍነህ ፡ ልታበላሽ ፡ አካል ፡
ሲኒማ ፡ በማለት ፡ የምትሐት ፡ ትዕይንት ፡ በማዘጋጀትህ ፡
የፍሪዝ ፡ ዲቃላ ፡ ዊልያም ፡ የተባልከው ፡ ይህን ፡ በመ
ሥራትህ ፡
የሮም ፡ ግማሽ ፡ እግዜር ፡ ለመሥዋዕቱ ፡ ያርግህ ።
ዓለም ፡ የጠላውን ፡ ሕዝብ ፡ ያረከሰውን ፡ ያንን ፡
ብላሹን ፡ ሰው ፡
በዘመናት ፡ መኻል ፡ ግዑዝ ፡ እሱነቱን ፡ ትውልድ ፡ እን
ዳይረሳው ፡
በምስሉ ፡ ትይታ ፡ ተጠብቆ ፡ እንዲኖር ፡ ርዝራዥ ፡
ግብሩ ፡ የገማ ፡ ትዝታው ፡
እንዲሆን ፡ አስበህ ፡ ከሆነ ፡ አጅሬ ፡ ጂኦቫኒ ፡ ባቲስታ ፡
ካሜራ ፡ መሥራትህ ፡
እኛ ፡ ኑራ ፡ ሁሴን ፡ በረካነት ፡ ይንሱህ ።

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ስናየው ፡ የኖርነው ፡
ሲነድ ፡ ሲቃጠል ፡ የሚሥቅ፡ እሳት ፡ ነው ።

ያላንዳች ፡ ተውህቦ ፡ ያለምንም ፡ ጥናት ፤
ጽሑፍን ፡ በማቅረብ ፡
የግልን ፡ቂም ፡ ይዞ ፡ ለንዋይ ፡ አልሞ ፡ በዲቃላ ፡ ቋንቋ ፡
ወሬን ፡ ለመተብተብ ፡

ጋዜጣ ፡ መጽሔት ፡ በሚለው ፡ ባልትና ፡ መርዝን ፡
ለመመገብ ፡
ማንም ፡ ብዕር ፡ ጨባጭ ፡ እየቦጫጨረ ፡ ሀገር ፡ ለማሰደብ፡

ደራሲ ፡ ነኝ ፡ ያልከው ፡ ክሽኑ ፡ እንቶኔ ፡ ድርሰትን ፡ ለመ
ጻፍ ፡ አርአያ ፡ ስለሆንህ ፡
ያቧሬው ፡ ቃልቻ ፡ ንጹህ ፡ ደም ፡ ያስተፋህ ።
በአፍሪቃ ፡ አፈር ፡ ላይ ፡ ጭቆና ፡ ድንኳንን ፡ ዘር

ግተህ ፡ ያለኸው ፡
ያፈሩን ፡ ተወላጅ ፡ የአፈሩን፡ አምሳል፡ ያንን ፡ አፍሪቃዊ ፡
ካፊር ፡ ደባልቀኸው ፡

በአፖርታይድ ፡ ጅራፍ ፡ በረሀብ ፡ አለንጋ ፡ በጭቆና ፡
መጋዝ ፡ ገርፈኸው ፡ አርደኸው ፡
ባሳየኸው ፡ ሥቃይ ፡ አፍሪቃ ፡ እናቱን ፡ አንቅሮ ፡ እንዲ
ተፋት ፡ ሕጻን ፡ ሸማግሌው ።
በሸምቅ ፡ ዓላማህ ፡ በአረሚ ፡ ግብርህ ፡ ስለገፋፋኸው ፡
ይህን ፡ በማድረግህ ፡ አንተ ፡ የሰው ፡ ሰይጣን ፡ የባሕር ፡
ጋንጩራ ፡ ፕሪቶሪያ፡ ያለኸው ፡

የሮዴሺያው ፡ ስሚዝ ፡ ሌላ ፡ አልልህም ፡ ይሁዳ ፡
ሚስ ፡ ሰው ።

ከጥንት ፡ ጀምረን ፡ ስናይ ፡ እንደኖርነው ፡
ሲነድ ፡ ሲቃጠል ፡ የሚሥቅ ፡ እሳት ፡ ነው ።

በስበብ ፡ አስባቡ ፡ ራስን ፡ ለመጥቀም ፡
ንብረት ፡ ለማደርጀት ፡ እያጋነኑ ፡ ስም ፡
በሕግ ፡ አመካኝቶ ፡ እየተወጠ ፡ ቂም ፡
ደግሞም ፡ ለመፈንጠዝ ፡ በማዕዘን ፡ ዓለም ፡
ጭቆና ፡ ባርነት ፡ አድልዎና ፡ ዓመፅ ፡ እንዲስፋፉ ፡በጣም ፡



እንዲሆን ፡ ከሆነ ፡ አስበው ፡ መርምረው ፡ ሥልጣንን ፡
የሠሩት
ደግሞም ፡ አስተዳደር ፡ ሕግም ፡ ሆነ ፡ መንግሥት ፡
እነዚያ ፡ ጅጂዎች ፡ የዋሆቹ ፡ ፍጥረት ፡
ፕሌቶ ፡ አሪስቶትል፡ ሁላቸው ፡ ሊቃውንት ፡
ይህን ፡ ግብዝ ፡ ሐሳብ ፡ ከግብ ፡ ሳያደርሱት ፡
በሥራ ፡ ላይ ፡ ሳይውል ፡ ገና ፡ ሲወጥኑት ፡
ይሻላቸው ፡ ነበር ፡ አፎቿን ፡ ከፋፍታ ፡ ብትውጣቸው ፡
መሬት ።

ስለሌላው ፡ በደል ፡ ምሳሌ ፡ እንዲሆንህ ፡ ብትፈልግ ፡
ለማወቅ ፡
ወርደህ ፡ ወደ ፡ ቆላ ፡ ቮርስተርን ፡ ጠይቅ ፡
ያንን ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ ፡ የአጋንንቱን ፡ ሊቅ ።

ከድሮ ፡ ጀምሮ ፡ ባንክሮ ፡ እንዳየነው ፡
ሲነድ ፡ ሲቃጠል ፡ የሚሥቅ ፡ እሳት ፡ ነው ።
ያልተደረገውን ፡ ከዕንፍ ፡ እስከ ፡ አድማስ ፡
ጊዜን ፡ ጊዜ ፡ ገጭቶት ፡ ይወልደው ፡ ይመስል ፡ መዋቲ
ውን ፡ መንፈስ ፡

ከቶ ፡ መመሥረትህ ፡ በደል ፡ ለማጽደቂያ ፡ የውሸት ፡
ምክር ፡ ቤት ፡
በተስማምቻለሁ ፡ ለማድለብ ፡ ከሆነ ፡ የሰዎችን ፡ ሙክት ፡
ጮማ ፡ ለማይወጣው ፡ ከአኞ ፡ በስተቀር ፡ ልፋጭ ፡ ሊያ
በረክት ፡
አስበህ ፡ ከሆነ ፡ እንዲያ ፡ እንዲያ ፡ ማድረግህ ፡ የሰው ፡
ልጅ ፡ ለማወክ ፡
መንጋ ፡ ማጎሪያውን ፡ ፓርላማ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ለኛ ፡ ስላ
ሳለፍክ ፡

ያንግሉ ፡ ሳክሶኑ ፡ ለፍዳዳው ፡ ዊልያም ፡ ዘርህ ፡ አይባረክ ።
የዕንባ ፡ አምላክ ፡ ይመስል ፡ ዋይታ ፡ ሊከለክል፡
እንደ ፡ አሪት ፡ ጣዖት ፡ ግንቦትን ፡ ጠብቆ ፡ ደም ፡ ግብርን ፡
ሊቀበል ፡
ወይም ፡ እንደቆሪጥ ፡ መሥዋዕት ፡ ሊያነፈንፍ ፡ ከተማሪው፡
አካል ፡

አስበው ፡ እንደሆን ፡ የሙንጣዙን፡ አቋም ፡ ሀ ብለው ፡
ሲሡሩ ፡
ለኛ ፡ አይሆንምና ፡ ይመንገል ፡ ይመገበር ፡ ይነቀል ፡
ከሥሩ ።
የናዚው ፡ ጁስታፖ፡የሙሶሎኒ፡ኦቭራ ፡ ትገዛታው ፡
ሲል ፡ አለሁ ።
ለዘመኑ ፡ ሰዎች ፡ ያ ፡ ብቻ ፡ ለሥቃይ ፡ አይበቃም ፡
ብላችሁ ፡
የሹምባሽ ፡ ህላዌን ፡ ባልቅትትነት ፡ ምግባር ፡ በማቋቋ
ማችሁ ፡
የጥንቱ ፡ ግሪኮች ፡ በጎልጎታ ፡ ውስጥ ፡ ዓዕማችሁ ፡ እን
ዳለ ፡ ምድራቱ ፡ ትትፋችሁ ።

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እኛ ፡ እንዳየነው ፡
ሲቃጠል ፡ የሚሥቅ፡ ዘለዓለም ፡ እሳት ፡ ነው ።

ባንድ ፡ አልሆንም ፡ ብለው ፡ አንድነት ፡ እንዲያጡ፤
አንዳንድ ፡ ወስላቶችን ፡ በጎማ ፡ ወረንጦ ፡ ስታቆናጥጡ ፡
ከሾክ ፡ ኀሊና ፡ ላይ ፡ የጠመቃችሁት ፡ ጥንስሳችሁ ፡
ፈልቶ ፡ በኃይል ፡ ሲኮመጥጥ ፡
ዝቃጩ ፡ አተላ ፡ ገምቶ ፡ ሲከረፋ ፡ ያ ፡ የናንተው ፡ ብጥ
ብጥ ፡



ትግል ፡ ቅጥ ፡ እንዲያጣ ፡ ተውሣክ ፡ የሆናችሁ ፡
ኢምፔሪያሊስቶች ፡ ኰሎኒያሊስቶች ፡ ደቂቀ ፡ ችችሊ ፡
ፋሽስቶች ፡ ሁላችሁ ፡
የኑክሊየር ፡ ነፋሪት ፡ አንድዶ ፡ አቃጥሎ ፡ ቀቅሎ ፡ ይፍ
ጃችሁ ።

ምናምንቴ ፡ እንዲልስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ትል ፡ አርጋ
ችሁ ፡ ልትፈጥሩት ፡
ያላንዳች ፡ ማጣጣም ፡ የሚቀርብለትን ፡ እንዲምግ ፡እን
ዲጋት ፡
የዕውቀትን ፡ አምባ ፡ የመንፈስን ፡ አድባር ፡ ለንዋይ ፡
ልትሸጡት ፡

ዘላቂ ፡ ኅሊናን ፡ ቱር ፡ አርጎ ፡ በማጠብ ፡ በነጭ ፡ ለማስ
ቀረት ፡
የማወቅን ፡ ዋጋ ፡ በአእምሮ ፡ ሳይሆን ፡ በሌጣ ፡ ብራና ፡
ሰውን ፡ ለመለካት ፡
ለንደዚህ ፡ ያለ ፡ ግብ ፡ ከሆነ ፡ አስባችሁ ፡ ዩኒቬርስቲ
ውን ፡ ድሮ ፡ ስታቆሙት፤
የጥንቶቹ፡ ጅሎች ፡ ጊዜ ፡ የዋጣችሁ ፡ ያውሮፓ ፡ ቀሳውስት
ይህን ፡ ሥራችሁን ፡ አይቶ ፡ የማያልፈው ፡ አምላክ ፡
አማልክት ፡
በኋለኛው ፡ ኑሮ ፡ ተካፋይ ፡ ያርጋችሁ ፡ ከዲያብሎስ ፡
መንግሥት ፡ ከሣጥናኤል ፡ ሕይወት ።

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እኛ ፡ እንዳየነው ፡
ሲቃጠል ፡ የሚሥቅ ፡ ዘለዓለም ፡ እሳት ፡ ነው።

ስለድምሩ ፡ ሕዝብ ፡ ስለተራው ፡ ምሁር ፡ ትን
ሣኤና ፡ድቀት ፡ ከመፈላሰፉ ፡
መናገር ፡ ቢያስፈልግ ፡ ስለነሱ ፡ ጠባይ ፡ ደግም ፡ ሆነ ፡ክፉ፤

«ዝልፎሙ ፡ ለከለባት» እንዳለው ፡ መጣፉ ፡
«እለ ፡ ገመለ ፡ ይውህጡ ፡ ወጸጼተ ፡ ይነጥፉ ፡»
በሚለው ፡ ቃል ፡ ዘግተን ፡ ይሻላል ፡ ማለፉ ።
ደግሞስ ፡ የሌሎቹ ?

ረቂቃን ፡ ሆነው ፡ መርገም ፡ አሸታቾቹ ።
አዎን ፡ ነጻነትና ፡ ፍርድ ፡ መብትና ፡ ሰላም ፡
ፈርጥጠው ፡ የመጡ ፡ ናቸው ፡ ከሌላ ፡ ዓለም ፡
በጠፈር ፡ ቀዳዳ ፡ ሾልከው ፡ ያመለጡ ፡ ወንጀለኞች ፡ በጣም
ስማያዊ ፡ ሽፍቶች ፡ ሳይሆኑ ፡ አይቀሩም ።
የነዚህን ፡ ቃላት ፡ ተግባራዊ አቋም ፡
ሀገሮች ፡ ሳንመርጥ ፡ ባለስካም ፡ ካምቻትካም ፡
በያለበት ፡ ሥፍራ ፡ እየዞረን ፡ ብናይም ፡
በምድራችን ፡ ዓለም ፡ ስፍራ ፡ የላቸውም ።

የሰማይና ፡ የምድር ፡ ልሳናት ፡ ተጋጭተው ፡
በሽታ ፡ ሆኖናል ፡ ውጤቱ ፡ ጦሳቸው ።
የኪሩቤልና ፡ የሡራፌል ፡ ቋንቋ ፡
ሽፍታ ፡ ሆኖ ፡ ዘምቶ ፡ ልሳን ፡ እያንቋቋ ፡
ይጫወትብናል ፡ በኛ ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡
መኖር ፡ የበደለን ፡ ያልታደልን ፡ ፍጡሮች ።
በመንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ቅዱሳን ፡ መላእክት ፡
የሚጠቀሙበት ፡
በረቂቅ ፡ ዩቶጵያ ፡ ኅቡዓን ፡ ፍጡሮች ፡ የሚሞካሹበት ፡
በተፈጥሮ ፡ ያለው ፡ እውነተኛው ፡ ሕይወት ፡ እንዳለ ፡
ካለበት ፡
ኑሮአቸው ፡ ከዚያ ፡ ነው ፡ መብትና ፡ ሰላም ፡ ፍርድና ፡
ነጻነት ፡
ምድራውያን ፡ ናቸው ፡ እያልን ፡ በማሰብ ፡ በከንቱ ፡
አንዘብት ።



ስለዚህ ፡ ነጻነትና ፡ ፍርድ ፡ መብትና ፡ ሰላም ፡ ሁሉም ፡
በጠቅላላው ፡
ጀሀነም ፡ ይውረዱ ፡ በኃይል ፡ ተንኮታኩተው ፡
አጥፍተዋልና ፡ የደገኛን ፡ ሕይወት ፡ አድማ ፡ ሤራ ፡
መተው ፡
ለአምባገነኑ ፡ ጉልበት ፡ ለተጫነው ፡ ረድተዋልና ፡ እን
ዲያ ፡ እንዲያ ፡ ሳለው ፡ ሰው ።
ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ስናይ ፡ እንደኖርነው ፡
ሲቃጠል ፡ የሚፈግ ፡ እሳት ፡ ብቻ ፡ እኮ ፡ ነው ።
ደግሞስ ፡ የእንስሳቱ ፡
ምን ፡ ነበር ፡ ጥፋቱ?
ሊያስረግም ፡ የሚችል ፡ እንደሳይንቲስቱ !
አዎን ፡ የተፈጥሮሽ ፡ ሆኖ ፡ የራስሽን ፡ ነጣቂ
ላሚቱ ፡ የዋሒት ፡ ማሰብ ፡ የማታውቂ ፡
እንዲያው ፡ ለመሆኑ ፡ ሣሩን ፡ በመገተም፡ ውሀውን ፡ በመ
ጋት ፡ የደከምሽበትን ፡
ቅቤሽን ፡ ወተትሽን ፡ እርጎሽን ፡ አይብሽን ፡
ለሆዳሙ ፡ ክፍል ፡ ለዚያ ፡ ለጅብቲው ፡
ለከርሡ ፡ አስበሽ ፡ ምግብ ፡ እንዲሆነው ፡
ከጥጃሽ ፡ በመንጠቅ ፡ ስጦታ ፡ ስላረግሽ ፡ እንደዚያ ፡
ኅልው ፡ ሰው ፡
የአሎባሩ ፡ ማጥ ፡ እግርሽን ፡ ይሰበረው ፡
ያቺ ፡ ሽህ ፡ አንበሶም ፡ ጡትሽን ፡ ታድርቀው ።
ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ስናይ ፡ እንደኖርነው ፡
ሲቃጠል ፡ የሚሥቅ ፡ እሳት ፡ ብቻ ፡ እኮ ፡ ነው ።
ደግሞስ ፡ የንቢቱ ፡ የዚያች ፡ የበራሪ ፡
ያልተመቻት ፡ ለታ ፡ የትም ፡ ጕር ፡ አዳሪ ፡

እኔ ፡ ታዛቢሽ ፡ ነኝ ፡ እቅጩን ፡ ልንገርሽ ፡
ገናና ፡ ብትባይ ፡ በታታሪነትሽ ፡
ዓለሙ ፡ በመላው ፡ አዳሜ ፡ ጠቅላላው ፡ በውሸት ፡ አድ
ንቆ ፤ ሕይወቱም ፡ ቢያደርግሽ ፡

ለከርሣሙ ፡ ክፍል ፡ ለነሆድ ፡ አላሁ ፡ ምስጋና ፡ ለሌለው ፡
ጣዕም ፡ ለማያውቀው ፡ ማርሽን ፡ በመስጠትሽ ፤
አርባ ፡ አራቱ ፡ ታቦት ፡ ለእልፍ ፡ ይሰንጥቁሽ ።
የጫጨቶች ፡ አያት ፡ ባልቴቷ ፡ ዶሮ ፡ ሆይ ፤
ጭረሽ ፡ ያፈራሽው ፡ የገዛ ፡ ገንዘብሽ ፡ ዕንቍላሉ፡ ልጅሽ ፡
ሆኖብናል ፡ በዳይ ።

በራስሽ ፡ ውዴታ ፡ በለጋሥ ፡ ጥረትሽ ፡ በገፍ ፡ እየሰ
ጠሽ ፡ ለሆዳሙ ፡ ክፍል ፤
ልቡን ፡ በማሳበጥ ፡ እንዳያስብ ፡ አርገሽ ፡ ለፈጸምሽው ፡
በደል ፤
ክንፍሽን ፡ ይሰበረው ፡ የእየሩ ፡ ጋኔል ።

ከድሮ ፡ ጀምሮ ፡ ሲታየን ፡ የኖረው ፡
ሲነድ ፡ ሲቃጠል ፡ የሚሥቅ ፡ እሳት ፡ ነው ።

ለፈጸሙት ፡ ተግባር ፤ ቡራኬ ፡ ለመስጠት ፡ ቢያስፈ
ልግ ፡ በውነት ፤
መመረቅ ፡ ዝንብን ፡ ነው ፡ ደግሞም ፡ ብርቱዎቹን ፡
አንዳንዱን ፡ ደዊያት ።

አዎን ፤ አንቺ ፡ ያገሬ ፡ ዝንብ ፡ የሰይጣን ፡ ንቢቱ ፤
ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ አዳሜ ፡ ሲሰድብሽ ፡ ያላግባብ ፡ በከንቱ ፤
ሙያሽን ፡ ሳያውቀው ፡ ያላንዳች ፡ ምክንያት ፡ እንዲያ ፤
ሲጠየፍሽ ፡ በደነዝ ፡ ስሜቱ ፡



አንቺ ፡ ግን ፡ በውነት ፤ ለውነት ፡ ስትይ ፤ ሐሞትሽን ፡
ኮስትረሽ ፡ ስለኖርሽ ፡ በድካም ፤
የሀገር ፡ ጭንትን ፡ የብሔር ፡ ሽክምን ፡ የወገን ፡ አላልን ፤
አርጋጁን ፤ አንጓጁን ፡ ለማጥፋት ፡ ለማውደም ፤
ጠንቃዊ ፡ ነፍሳቱን ፡ ጀርሙን ፡ ትላትሉን ፤ ከዳሪ ፡ ወደ
ቤት ፡ ስታመላልሽ ፤ ለፈጸምሽው ፡ ጀብዱ ፤
አምላክ ፡ ተመልክቶ ፤ በኪነ ፡ ጥበቡ ፤ ሳምሶንን ፡ ያር
ግሽ ፤ በለጋሥ ፡ ልማዱ ።
አሜባ ፤ ደም ብዛት፤ የሳምባ ፡ ነቀርሣ ፤ ውጋትና ፡
ቁርጠት ፡ ደዊያት ፡ ሁላችሁ ፤
ሰው ፡ ያልሆነውን ፡ ሰው ፤ ከሰዎች ፡ መርጣችሁ ፤
ለማጥፋት ፡ ለማውደም ፡ እግዜር ፡ ያበርታችሁ ።

ከድሮ ፡ ጀምሮ ፡ ባድናቆት ፡ ያየነው ፡
ሲነድ ፡ ሲቃጠል ፤ የሚሥቅ፡ እሳት ፡ ነው ።

በመጨረሻ ፡ ላይ ፡ ለመውቀስ ፡ የምሻው ፤
እግዚአብሔርን ፡ ሳይሆን ፤ ያንን ፡ ተፈጥሮ ፡ ነው ፡
ከትእዛዙ ፡ አልፎ ፤ ሕግጋቱን ፡ ጥሶ ፤ ያላግባብ ፡ የሠራው ።

ፀሐዩን ፡ አየሩን ፤ ምክንያት ፡ አድርገህ ፤
በወንዝ ፡ በተራራ ፤ ጥንት ፡ ያልነበረውን ፤ መንደሮችን ፡
ፈጥረህ ፤
ትግሬና ፡ ጉራጌ ፤ አማራና ፡ ጋላ ፤ ሽናሻና ፡ ዶርዜ ፤ በማ
ለት ፡ ሸንሽነህ ፤
ሐጎስና ፡ ጭሎ ፤ ለማና ፡ ዋኬኔ ፤ ዶጮቴ ፡ ፋጢማ ፤ የሚል ፡
ዘዬ ፡ አውጥተህ ፤
በቋንቋ ፡ በልማድ ፤ ባልባሌ ጠባይ ፤ በኾርጉርጉር፡ መንፈስ ፡
ያላግባብ ፡ ከፋፍለህ ፡

ተገንጥሎ ፡ ሊኖር ፤ የማይቻለውን ፤ ተቻይ ፡ በማስመሰል ፡
ልዩ ፡ ነገድና ፡ ጎሣ ፡ በመሥራትህ ፤
ቃዲውን ፡ ከቄስ ፡ ጋር ፤ በምትሐት ፡ ማስረጃ ፤ በእምነት ፡
ለያይተህ ፤

አንደኛውን ፡ ብሩህ ፤ ሌላውን ፡ ጥሩሩ ፤ አንዱን ፡ ባለዞማ ፡
አንዱን ፡ ባለሽምብር ፤ ደደብና ፡አዋቂ ፤ እንዲያ፡
እንዲያ ፡ አድርገህ ፤
የማይገታውን ፡ የዘመት ፡ ግዴታ ፡ በያንዳንዱ ፡ ሰው ፡
ላይ ፡ ከንትኑ ፡ ለጥፈህ ፤
ይህን ፡ የመሰለው ፤ ብናኝ ፡ ሽርፍራፊ ፤ የተፈጥሮ ፡ ሕግህ ፡
ያለም ፡ ፍልስፍናህ ፤ ደደብ ፡ ስላሰኘህ ፡
ተፈጥሮ ፡ አማትክን ፡ ባለጌ ፡ ዳኛ ፡ ነህ ።

ምድርም ፡ በበኩልሽ ፡ ሰው ፡ ያልሆነውን ፡ ሰው፡
አቅፈሽ ፡ በመኖርሽ ፡
ያንን ፡ ትልቁን ፡ ትል ፤ ዳዊትና ፡ ዳርዊን ፡ ምስክሩ ፡
ሆነው ፤ ሰው ፡ አለመሆኑን ፡ በደንብ ፡ ያብራሩልሽ ፡
ምነው ፡ የጽድቅ ፡ አላህ ፡ አምላክ ፡ አማልክት ፤ ከየብስ
ነት ፡ ይልቅ ፤ ውሀ ፡ አርጎ ፡ ባስቀረሽ ።

አልሰማሽ ፡ እንደሆን ፤ አልገባሽ ፡ እንደሆን ፤ ምድር ፡
የኛ ፡ አዳራሽ ፤
ስላቀፍሽው ፡ ፍጡር ፡ ያለውን ፡ ዓላማ ፡ ምናምንቱ ፡
ሐሳብ ፤ አንዳንዱን ፡ ልንገርሽ ።

አዎን ፤ እንዲህ ፡ ይልልሻል ፤
ካፈርሽ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፤ ኋላም ፡ አፈር ፡ ሲሆን ፤ የሚሆንሽ ፡
አካል ።
«- - - ደሀ ፡ ጌታ ፡ ሆኖ ፡ ለመጥገብ ፡ ከበቃ ፤
የቁንጫ ፡ አንጀት ፡ ማንን ፡ ተመግቦ ፤ እንደምን ፡ ይጠርቃ?



የቤታችን ፡ ጽዳት ፡ በሥርዓት ፡ ቢጠበቅ ፡
ወገን ፡ የለሽ ፡ ቱሐን ፡ እንዲሁም ፡ ሸረሪት ፤ ከምን ፡
ቦታ ፡ ትውደቅ ?

ድሪቶ ፡ ቡቱቶ ፡ ልብሳችን ፡ ቢሻሻል
የቅማሎች ፡ ሕይወት ፡ ለምን ፡ ይበደላል?

ባለጫማ ፡ ሆኖ ፡ ሁሉም ፡ ካማረበት ፡
ደሀዋ ፡ ሙያሌ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ ይዋጣት?
እንዴትስ ፡ ይደፈር ፡ የቁንጫ ፡ መብት ?
ዝግጅቱ ፡ አምሮ ፡ ሁሉም ፡ እንዲደርሰው ፤ ትም
ህርት፡ ቢስፋፋ ፡

ለብዙ ፡ ዘመናት ፤ ከኖረበት ፡ ሀገር ፤ ዘመድ ፡ ድንቁርና ፡
እንዴት ፡ ድንገት ፡ ይጥፋ?
በሥራ ፡ ደርጅተን ፤ ሥልጣኔን ፡ ይዘን ፤ ገናና ፡ ብንባል ፡
ላያሌ ፡ ዓመታት ፡ ጠብቀን ፡ ያኖርነው ፡ ድህነት ፡ ባህ
ላችን ፡ ይቃወስብናል ።

የያንዳንዱ ፡ ጤና ፡ እንዲጠበቅለት ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡
ቢቋቋም ፡
ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ ትውልድ ፡ ያወረሰን ፡ የቆየው ፡ በድ
ካም ፡
በሽታ ፡ ቅርሳችን ፡ እንዴት ፡ ባንዴ ፡ ይውደም? - - -»
እንግዲህ ፡ ልጨርስ ፡ ርግማኔ ፡ ይብቃኝ ፡
ያለፈው ፡ ያረካል ፡ ለፍሬ ፡ ካለልኝ ።
ሆኖም ፡ ከመሔዴ ፡ በፊት ፡ አንድ ፡ ጥያቄ ፡ አለኝ ፤
እናንተ ፡ ሁላችሁ ፡ የምትመልሱልኝ ።
ኧረ ፡ ለመሆኑ ፡ እንዴት ፡ አድርገህ ፡ ነው ፡
ዓለምን ፡ ስታያት ?
እኔስ ፡ ግራገባኝ ፡ ያይንህ ፡ ውሀ ፡ ስሜት ።

የሥጋህን ፡ ስሜት ፤ ሰብ አዊ ፡ ኅሊናህ ፤ ተመራምሮ ፡
ሲያየው ፤
ንገረኝ ፡ ልረዳው ፤ አስረዳኝ ፡ ልወቀው ፤ ምን ፡ ይትበህል ፡
አለው ?

መጠኑ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ የዓይኖችህ ፡ ቅንድብ !
ወፍራም ፡ ነው ፡ ቀጭን ፡ ነው፡ ወይስ ፡ ሰፊ ፡ ጠባብ?
ማየት ፡ የተሳነው ፡ የስሜትን ፡ እባብ !

አላሳይ ፡ አለህ ፡ ወይ ፡ የብሌንህ ፡ መጥቆር ?
ስሜትህ ፡ እውነት ፡ መስሎ ፡ እየታየው ፤ ያደረገህ ፡ገባር ፤
ደግሞም ፡ ያስገደደህ ፤ ሆነህ ፡ እንድትቀር ፤ ያለማሰብ ፡
ዕውር !

በሥርዓት ፡ እንዳታይ ፤ እንቅፋት ፡ ሆነህ ፡ ወይ ፤ ያይኖችህ፡
ሽፋሽፍት ?
ታውረህ ፡ የቀረህ ፡ በስሜት ፡ እስር ፡ ቤት ፡
እንደፈለግሁ ፡ ልሁን ፤ የሚለው ፡ ኅሊናህ ፤ ሆኖህ ፡
የግር ፡ ብረት ።

ምን ፡ ይሆን ፡ ጠባዩ ፡ የዓይኖችህ ፡ ውሀ ?
በጣም ፡ ደስ ፡ የሚለው ፤ ጠቋመው ፡ ሲያሳዩት ፡ የስሜት ፡
በረሀ ።

ምን ፡ ይሆን ፡ ጠባዩ ፤ የጆሮህ ፡ ከበሮ ?
ለስሜት ፡ ባሕሪ ፤ ያረካል ፡ ተብሎ ፤ በተስፋ ፡ ሲመቱት ፤
በስብከት ፡ ሲያሻሹት ፡ የሚጨፍር ፡ አብሮ ።

እንዴት ፡ ይሆን ፡ ሥራው ፡ የምላስህ ፡ ሥጋ ?
ለርኩስ ፡ ስሜት ፡ ሲባል ፤ መራራ ፡ ሲሰጡት ፤ እሬቱን ፡
ሲያቀምሱት፡ለውጦ፡አጣፍጦ፡ የሚያደርገው ፡ ሸጋ ፡



ያፍንጫህ ፡ አሠራር ፡ ምን ፡ ይሆን ፡ ምሥጢሩ ?
ስሜትን ፡ ለማግነን ፡ ግማታሙን ፡ ሽታ ፡ ቀይሮ ፡ ሲያ
ደርገው ፡ ያለመጠን ፡ ጥሩ ።

እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ የተፈጥሮህ ፡ ጠባይ ፡
ለስሜት ፡ ከሆነ ፡ የመኖርህ ፡ ጉዳይ ፡
ችግርን ፡ ተደስት ፡ ደስታን ፡ ተሠቃይ ።
ግን ፡ ያሰብከው ፡ ዓላማ ፡ አልሆን ፡ ብሎህ ፡ ሲከሽፍ ፡
ሁኔታው ፡ ሲጠጥር ፡
ጠጣሩ ፡ እንዲላላ ፡ የላላውን ፡ ወጥር ።

በኔነቴ ፡ ክልል ፡ እናንተን ፡ አይቼ ፡ የናንተን ፡ ስናገር ፡
ላለመኖር ፡ መኖር ፡ ለመኖርም ፡ መኖር ፡
ላለመማር ፡ መማር ፡ ለመማርም ፡ መማር ፡
ለማግኘት ፡ መታገል ፡ ለማጣትም ፡ መጣር ፡
ለማትረፍ ፡ መዋተት ፡ ለመክሰርም ፡ መጋር ፡
ላለማሰብ ፡ ማሰብ ፡ ለማሰብም ፡ ማሰብ ፤ የኋላ ፡ ኋላ ፡
ግን ፡ እንደኳስ ፡ ለመንጠር ፡
ላለማወቅ ፡ ማወቅ ፡ ለማወቅም ፡ አውቆ ፤ በጥበብ ፡ ደር
ጅቶ ፡ በሀብታት ፡ ለመናር ፡
ይህ ፡ ነው ፡ ፍልስምናው ፡ የዘመኑ ፡ ነገር ፤ የጊዜያችን ፡
ታምር ፤

ሆኖብኛል ፡ ለኔ ፡ ዕውር ፡ እንቆቅልሽ ፡ የሰዎች ፡ አኗኗር ።
እንግዲህ ፡ ለዚህ ፡ ከሆነማ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ምርምር ?
ኅሊናን ፡ መሞረድ ፡ ለውነት፡ ሲቆጩ፡በውነት፡መማቀቅ ?
ታዲያኮ ፡ ንገሩኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ እውቀት ? ጥበብ፡
ፍልስምና ፡ እነሱን ፡ ለማንገሥ ፡ ባለው ፡ ጥረት ፡
መኻል ፡ በነሱው ፡ መዳቀቅ ፡
በረቂቅ ፡ አለኝታ ፡ ያሉበትን ፡ ትቶ ፡ ካሉበት ፡ ለመምጠቅ

ዘለዓለም ፡ መንፏቀቅ ፤ መንፏቀቅ ፤ መንፏቀቅ ፤
ቋቱ ፡ ጠብ ፡ ላይል ፤ ጎሊና ፡ ላይረካ ፤ እስከ ፡ መጨረሻው ፤
ሰውን ፡ ላለማወቅ ፤
ያንን ፡ ትልቁን ፡ ትል ፤ እጅ ፡ እግር ፡ ያለውን ፤ የሚፈ
ጥረውን ፡ ጠንቅ ።

ሆኖም ፡ ያዳሜ ፡ ልጅ ፡ ብትሰማኝ ፡ ተመክር ፡
የዳዋ ፡ ውስጥ ፡ አይጥ ፡ የሜዳው ፡ ኳንንቾር ፡
የቆንጥር ፡ ከርከሮ ፤ የደኑ ፡ ውስጥ ፡ አነር ፤
የመንደር ፡ ድምር ፡ ሕዝብ ፤ የበረሀው ፡ ነብር ፤
የጉድጓዱ ፡ አሸን ፤ የባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ አዞ ፤ የረግረጉ ፡
አልቅት ፤ የኩይሳው ፡ ቁጫጭ ፤ ያየር ፡ ጆፌ ፡ አሞራ ፤
ከቶ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፤
በደመ ፡ ነፍስ ፡ ኃይል ፤ የሚንቀሳቀሰው ፤ ጠቅላላውም ፡
ፍጡር ፤

አኘኮ ፡ አመንዥኮ ፤ ከርትሶ ፡ ደቁሶ ፤ አድቆ ፡ ሰልቆ ፤
ሰልቅጦህ ፡ እንዳትቀር ፤
አስብ ፡ ተመራመር ፤ ጠንቁል ፡ ተፈላሰፍ ፤ አጥብቀህ ፡
ተራቀቅ ፡ ላንተነትህ ፡ ስትል ፤ ሁኔታው ፡ ቢረቅም ፡
በዘመኑ ፡ ነገር ፤
ይህ ፡ ነው ፡ የገፋፋኝ ፡ ዛሬ ፡ ለመናገር ።
«ነቀፌታ ፡ ቀርቶ ፤ ድራሽ ፡ አባቱም ፡ ጠፍቶ ፤ ስሕተት ፡
እንዳይቀጣ ፤
አንዳንድ ፡ ከፉ ፡ ሰዎች ፤ ባለንበት ፡ ሀገር ፤ ባለንበት ፡
ዘመን ፡ አደራ ፡ እንዳናጣ»
የሚለው ፡ አዛውንት ፤ በዚህ ፡ ባድባራችን ፤ቀኍጥሩ ፡ ቢያ
መዝንም ፡
እኔስ ፤ በበኩሌ ' ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፤ ሰው ፡ የተባለውን ፡
ስሙን ፡ አላነሣም ።



ለመርገም ፡ ተፈጥሮ ፤ ተረግሞ ፡ ያለውን ፤ መርገም ፡ ላይ
መልሰው ፤ ሁለተኛ፡ አልረግምም ።
የሆነውን ፡ ሆኖ ፤ እንደሆነ ፡ ይኑር ፤ ለዓለመ - ዓለም ።
«በቃኝ»